# የብቃት ማረጋገጫ ያላቸው የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ዝርዝር

**Certified Home Care Aide Checklist**

Washington State Department of Social & Health Services — Transforming lives

**የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድርጅቶች ፣ የጎልማሳ ቤተሰብ ቤቶች እና ድጋፍ የሚደረግላቸው የመኖሪያ መገልገያዎች**

**የህግ መስፈርቶች:**

ከተቀጠሩበት ቀን ጀምሮ በ120 ቀናት ውስጥ የ75 ሰአታት ስልጠና (የ5 ሰአታት ገለጻ እና ደህንነትን ጨምሮ) ማጠናቀቅ እና በተቀጠሩ በ200 ቀናት ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ ያለው የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ መሆን አለብዎት። እነዚህን ሊፈጸምበት የተቀመጡ የግዜ ገደባትን ሟሟላት ካልቻሉ እየተከፈለዎት መቀጠል አይችሉም፡፡ የሚፈለገውና የተቀመጡ የጊዜ ገደቦችን ለመጠቀም የሚከተሉትን ተመራጭ የሆኑ የጊዜ መስመሮች እና ዝርዝሮች ይጠቀሙ።

## የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ ለመሆን ከቀጣሪዎት ጋር ይሙሉ።

| | እርምጃ:- | ማስታወሻዎች | ✔ |
|---|---|---|---|
| ቅደም ተከተል 1: | በኮንትራት ሰዓት ሙሉ ስምና የትውልድ ቀን ዳራ ማረጋገጥ የኋላ ታሪክ ምርመራ - BCCU ድህረ-ገጽ | ለሁሉም ቅፆች ተመሳሳይ ስም ይጠቀሙ፡፡ ምሳሌ: ዮናታን፤ ዮህንስ ወይንም ጆኒ | ☐ |
| ቅደም ተከተል 2: | የጉዳዩ መነሻ ድርጅት ቁጥር(OCA#) የሚባለው የመከታተያ ቁጥር ይወጣ እና ውሉ ሲደረግ በሚያገኙት የጣት አሻራ ቀጠሮ ፎርም ላይ ይጻፋል: : ይህንን ፎርም ይያዙ እና እዚህ ጋር OCA# ይጻፉ: ________________________ | **ይህም ለጤና ክፍል** (DOH) **ማመልከቻዎት** የሚፈለግ ሊሆን ይችላል፡፡ | ☐ |
| ቅደም ተከተል 3: | የጣት አሻራዎ ወዲያውኑ እንዲወሰድ ዝግጅት ያድርጉ፡፡ የቀጠሮውን ሰዓት እዚህ ላይ ይመዝግቡ: ___________ | የቀን መቁጠሪያዎትን ምልክት ያድርጉ! | ☐ |
| ቅደም ተከተል 4: | ✸ **እንክብካቤ ከመስጠትዎ በፊት:** የገለጻ (2 ሰአታት) እና ደህንነት (3 ሰአታት) የስልጠና ትምህርቶች ያጠናቁ። ለነዚህ ትምህርቶች የስልጠና የብቃት ማረጋገጫዎች ያስፈልግዎታል። የተፈቀደለትን መምህር ለማግኘት ስልጠና ከሚለው ስር ከዚህ በታች ይመልከቱ፡፡ | እነዚህ የምስክር ወረቀቶች የ 75 ሰዓት የስልጠና መስፈርት አካል ይሆናሉ፡፡ **መሰረታዊ ስልጠናውን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገው 120 ቀናት** መቁጠር የሚጀምረው ከተቀጠሩበት ቀን ነው። | ☐ |

## ለመረጃነት እና ፈተና የጤና መምሪያ ማመልከቻን ያቅርቡ

| | እርምጃ:- | ማስታወሻዎች | ✔ |
|---|---|---|---|
| ቅደም ተከተል 1: | **በተቀጠሩ በ14 ቀናት ውስጥ እንዲተገበሩት የሚመከር:-** የጤና ክፍል **HCA ማመልከቻ** እሽግ፡፡ የጽሁፍ የእውቀት እና ክህሎት ፈተና ለመውሰድ የሚያስችሎትን መረጃ የፕሮሜቲክ መመርመሪያ ከማመልከቻዎ ይቀበላል፡፡<br><br>ለ DOH እና ፕሮሜቲክ ተግባቦት በትንሹ አንድ የኤሜይል አድራሻ ማቅረብ ይገባዎታል፡፡ **DOH ከፕሮሜትሪክ ከመገናኘቱ በፊት ሁሉም ሰነዶች፣ የስልጠና ማጠናቀቂያ ማስታወሻ እና ክፍያዎች መፈጸማቸውን DOH ግድ ይላል፡፡** | ማመልከቻዎን በ14 ቀናት ውስጥ ካላስገቡ የመፈተን እድልዎ ይቀንሳል ወይም በቀነ ገደብዎ ማረጋገጫ ላያገኙ ይችላሉ፡፡<br><br>DOH አንድ ግዜ ማመልከቻዎን የተቀበለ እንደሆነ ባለ 10 አሀዝ DOH መረጃ ይሰይምልዎታል፡፡<br><br>በ (360) 236-2700 ላይ የ HCA መረጃ አስተባባሪን ሲያገኙ ወይም ከ DOH በቀጥታ የመረጃ መረብ መረጃ ሲያገኙ ይህንን ቁጥር ይጠቀሙ፡፡ | ☐ |
| ቅደም ተከተል 2: | ✸ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃትዎ ውሱን (LEP) ከሆነ ማለትም እንግሊዝኛ የማንበብ፣ የመጻፍ ወይም የመናገር ችሎታዎት ውሱን ከሆነ ለተጨማሪ የ60 ቀናት የጊዜያዊነት የብቁነት ማረጋገጫ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። | LEP ብቻ: በ DOH ማመልከቻዎ ላይ ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት እንደሚፈልጉ ምልክት ያድርጉ: : | ☐ |
| ቅደም ተከተል 3: | በእስፓኒሽ፤ በራሽይኛ፤ ቬትናም፤ ኮሪያ ቻይንኛ፤ ካምቦድያ፤ ሉኣቲንያ፤ ሳሞኣን፤ ሱማሊኛ፤ ዩክሬን፤ ታጋሎግ፤ አማሪኛ፤ ወይንመ በአረብኛ የ HCA ፈተና ለመውሰድ በ HCA ፈተና ማመልከቻ ላይ የቋንቋ ፈላጎትዎን ያረጋግጡ፡፡<br><br>ከተዘረዘሩት ውጭ በሆነ ቋንቋ ፈተናውን መውሰድ የሚሹ ከሆነ፣ በፕሮሜትሪክ ድረ-ገጽ ላይ የፈተና አቅርቦቶች መጠየቂያ ፓኮ ፎረም በመሙላትና በፎርሙ ላይ ባለው አድራሻ በመላክ በራስዎ ቋንቋ የግል አስተርጓሚ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ | የአስተርጓሚ/ የአቅርቦት ጥያቄ 30 ቀናት ሊወስድ ይችላል፡፡<br><br>ለማረጋገጥ እርስዎ ምላሽ መስጠት የሚገባዎት DOH ኢሜይል ይልክሎታል፡፡<br><br>ስልጠናዎን እንደፈጸሙ በየዕለቱ ከDOH እና ፕሮሜትሪክ የሚላከልዎት ኢንቦክስ፣ ጀንክ እና ስፓም ማህደር ይመልከቱ፡፡ | ☐ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቅደም ተከተል 4፡ | የ DOH ማመልከቻ ክፍያውን እና የ Prometric ፈተና ክፍያውን ለ DOH ይላኩ። **ማሳሰቢያ፡- ስልጠናው የሚቀርበው በስልጠና አጋሮች ከሆነ ክፍያዎችን አይፈጽሙ እና በማመልከቻው ላይ በማመልከቻ ግዜ የሚከፈል የሚለው ላይ ምልክት ያድርጉ፡፡** | ከማልከቻዎር ጋር ቼክ ወይም መኒ ኦርደር ይላኩ። | ☐ |

## ለስልጠና ይመዝገቡ

| | እርምጃ፡- | ማስታወሻዎች | |
|---|---|---|---|
| ቅደም ተከተል 1፡ | **✹ በተቀጠሩ በ14 ቀናት ውስጥ፡**<br>ለ 70 ሰዓት መሰረታዊ ስልጠና ይመዝገቡ፡፡ | ትምህርት/አስተማሪ መፈለግ | ☐ |
| ቅደም ተከተል 2፡ | **✹ በተቀጠሩ በ60 ቀናት ውስጥ እንዲተገብሩት የሚመከር፡** በሚኖሩበት አካባቢ ክፍሎችን ማግኘትዎን ለማረጋገጥ የ 70 ሰዓት መሰረታዊ ስልጠናዎን ወዲያውኑ ያጠናቁ፡፡ | የፈተና እና የብቁነት ማረጋገጫ የጊዜ ገደቦችን እንዳያሳልፉ። | ☐ |
| ቅደም ተከተል 3፡ | አስፈላጊ የሆነውን የ 75 ሰዓት ስልጠና ያጠናቀቁ ከሆነ የቤት እንክብካቤ ድጋፍ (HCA) ፈተና ለመውሰድ ብቁ ይሆናሉ፡፡ | ለስልጠና ቀናት እና ወቅት የቀን መቁጠሪያዎ ላይ ምልክት ያድርጉ! | ☐ |
| ቅደም ተከተል 4፡ | የመጨረሻውን የ 75 ሰዓት መሰረታዊ ስልጠና በሚያስተምረው DSHS ማረጋገጫ የሰጠው መምህር የ 75 ሰዓት የማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ያገኙ፡፡ | ለአስተማሪው ሁሉንም የምስክር ወረቀቶች ያሳዩ። | ☐ |

## በፕሮሜትሪክ አማካኝነት የሚመረመር

| | እርምጃ፡- | ማስታወሻዎች | |
|---|---|---|---|
| ቅደም ተከተል 1፡ | የጽሁፍ የእውቀት እና ክህሎት ፈተና ይለፉ፡፡ የፈተናውን ቀንና ቦታ እዚህ ይፃፉ፡ ________________<br>የመጀመሪያ ፈተና የተሰጠዎትን ግዜ ከፕሮሜትሪክ ይውሰዱ፡፡<br>ፈተናውን የማለፍ እድልዎን ለመጨመር ፈተናውን ስልጠናው ማብቂያ ላይ ይውሰዱ፡፡ ኢሜይል ከ Pbt-admit@Prometric.com ይላካል፤ ጉዳዩ የሚለው መስመር ላይ የፈተና መረጃዎን፣ ስምዎን፣ የፕሮሜትሪክ መታወቂያ # ይይዛል(ኢንቦክስ፣ ጀንክ እና ስፓም መሀደሮችን ይመልከቱ)፡፡ | ፕሮሜትሪክ ከእርስዎ ጋር ግንኙነት የሚያደርገው DOH ማመልከቻ ላይ በገለጹት የኢሜይል አድራሻ ብቻ ነው፡፡<br>ስልጠናውን ባጠናቀቁ በ 14 ቀናት ውስጥ ከፕሮሜትሪክ የፈተና ቀን ኢሜይል ካልተቀበሉ 1-800-324-4689 ላይ ፕሮሜትሪክን ያግኙ፡፡ | ☐ |
| ቅደም ተከተል 2፡ | ሙከራውን ከወደቁ ወዲያውኑ ለፈተና ያስቀጥሩ፡፡ ፈተናውን እንደገና ለመውሰድ ፕሮሜትሪክን ወዲያውኑ ያግኙ፡፡<br>የወደቁትን ፈተና ድርሻ ሁለት ግዜ ይውሰዱ፡፡<br>ለያንዳንዱ ዳግም መፈተኛ ክፊያ መክፈል ይጠበቅብዎታል፡፡ | ስላንተ ማረጋገጫ መረጃ በ DOH ድረ-ገጽ Provider Credential Search (HM or PV) ላይ ይገኛል፡፡ እውቅናዎት ፈጣን (""Active")ካመለከተ፤ መስራት ይችላሉ፡፡ በጤና ክፍል ድረ-ገፅ ፈጣን ሳይሆኑ ከ200 ቀናት እላፊ መስራት አይችሉም፡፡ | ☐ |

| ኤጀንሲ | ስልክና ፋክስ | የፖስታ መላኪያ አድራሻ | ኢሜይል፡- |
|---|---|---|---|
| የጤና ክፍል (DOH) | **የጤና ክፍል ብቃት ማረጋገጫ አስተባባሪ (HCA Credentialing Coordinator)**<br>(360) 236-2700<br>**የጤና ክፍል ደንበኞች አገልግሎት**<br>(360) 236-4700 | **ማመልካቻውን የሚልኩት፡ (ክፍያ አያካቱ)**<br>DOH - Home Care Aide Credentialing<br>P.O. Box **1099**<br>Olympia, WA 98507-1099<br>**ከመጀመሪያው ማመልከቻ ጋር ያልተላኩ ሌሎች ሰነዶችና ይላኩ፡**<br>DOH - Home Care Aide Credentialing<br>P.O. Box **47877**<br>Olympia, WA 98504-7877 | **የጤና ክፍል ድረ-ገፅ**<br>የቤት እንክብካቤ ረዳት<br><br> |
| ፕሮሜትሪክ | **ስልክ ቁጥር፥**<br>1-800-324-4689<br>ጥያቄዎችዎን ለመመለስ እንዲረዳዎ የመረጃ ትንሽ መጽሀፍ (14 ቋንቋዎች) ያውርዱ፡፡ | **የፕሮሜትሪክ አድራሻ፡**<br>Attention: Washington Home Care Aide Program<br>7941 Corporate Dr.<br>Nottingham, MD 21236 | **ፕሮሜትሪክ ኢሜል፡**<br>WAHCA@prometric.com<br>**ፕሮሜትሪክ የድር ጣቢያ፡**<br>ፕሮሜትሪክ |

**የ HCA ፈጣን መገናኛዎች፡** www.adsa.dshs.wa.gov/professional/training/links ላይ መገናኛውን በአንድ ስፍራ ያግኙ